# ሰይጣናዊ አሳፋሪ አምልኮ በመስቀል አደባባይ!

በቅድሚያ መታወቅ ያለበት ኢሬቻ አምልኮ እንጂ ባህል አይደለም።ባልሰለጠነው ዘመን የሰው ልጅ ከችግሩ ለመዳን ሲጨንቀውና ሲጠበው በከባቢው ባለው ግዙፍ የተፈጥሮ ቁስ በሆነው ፣በወንዝ ፣በተራራ፣በዛፍ፣ከእንስሳትም በዝሆንና በመሳሰሉት ያምን ነበር እስከአሁንም ድረስ ይኸው አምልኮ አልቀረም።

ህንዶች፣ቲቤቶች፣ታይላንዶች____ ወዘተ በሂማልያ ተራራ፣በጋንጀስ ወንዝ በመሳሰሉት እያመለኩ ይጠመቃሉ፣ስጦታም ያቀርባሉ።የደቡብ አሜሪካና የአፍሪካ ህዝብም እንዲሁ ተመሳሳይ አምልኮ ነበረው፤ አሁንም አለው። በአገራችንም እንደዚሁ የተለመደ አምልኮ መኖሩ አይካድኖም።

የኦሮሞም ማህበረሰብ በከባቢው ባለው በሆራ ወንዝ፣በጨርጨር ተራራ፣በግዙፍ ዛፍ

እያመለከ  እየገበረና ቅቤ እየለቀለቀ በጭፈራና በፀሎት ሲያከብረው የነበረ ኋላቀር  አምልኮ ነው። የኦሮሞ ምሁራን ነን ባዮች ህብረተሰቡን ከእንዲህ አይነቱ አሳፋሪ አምልኮ ማላቀቅ ሲኖርባቸው እንደትልቅ እውቀትና ፀጋ የሚኮሩበት ከሆነ የእነሱም ንቃተ ህሊና ጥያቄ ውስጥ ይገባል።

የአምልኮን ነገር ካነሳሁ አይቀር ይችን ልጨምርና ልደምድም።በበርማና ላኦስ አካባቢ በሚኖሩ ጥቂት ማህበረሰቦች አይጥ ይመለከባታል።አመጣጡ ይህንን ይመስላል።ሰፈሩን ያመሰና ያስቸገረ አንድ ዝሆን ነበረ።ባልታሰበ ጊዜ ሞቶ አይጥ በላዩላይ ተቀምጣ በማየታቸው ዝሆኑን የገደለች፣ታምራዊና መለኮታዊ ሃይል እንዳላት በመቁጠር ሊመለከባት ቻለ።ከዚያ ወዲህ ትልቅ ክብረቀን ተመድቦ ለአይጦች ገፀበረከት የሚቀርብበት በዓል ይከበራል።አይጥም መግደል ሳይሆን ማባረር ትልቅ ሃጢያትና ወንጀል እንደሆነ ይቆጠራል።እምልኮ ካሉት እነዚህን ሁሉ አሳፋሪ፣ የኋላቀርነትና ድንቁርና ልማዶችን ያጠቃልላል። ኢሬቻንም ጭምር።

ከገረመው 16/07/2019